# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 55 ግንቦት 27 2001 ዓ.ም


"የኦባማ አስተዳደር በዚህ ህግ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ገዢዎች እያስተላለፈ ያለው መልእክት ....... "አሜሪካ ሲቪሉን ህዝባችሁን የሚያሸብሩትን ወታደሮች ታሰለጥኑ "ዘንድ አምስት ሳንቲም አትሰጣችሁም፤ ወይም ጦሩ ህዝቡን ይገልበት ዘንድ አንድም ጠብ መንጃ፣ አውሮፕላን፣ ታንክ ወይም መኪና አትሰጥም።" ማለቷ ነው

ፕሮፌሰረ አለማየሁ ገብረማሪያም

"በምንም ዓይነት መንገድ እርስ በርሳችን በመዘላለፍ የምናገኘው ጥቅም ስለሌለ፣ ለዚህ አይነቱ ፖለቲካ የምናባክነው ጊዜ የለም፤ ወቅቱ በጋራ እና በእልህ ተነስተን ነፃነታችንን የምናረጋግጥበትና አገራችንን የምንታደግበት ነው" ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ

## ልዩነቶቻችን አቻችለን በእልህና በጋራ አገራችን ለማዳን የምንነሳበት ጊዜ አሁን ነው ሲሉ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ጥሪ አቀረቡ

"ጊዜው፥ የሀገራችን ጉዳይ ያገባናል የምንል ወገኖች ክንዳችንን አስተባብረን በእልህና በህብረት የምንነሳበት እንጂ በጥቃቅን ልዩነቶች እርስ በርስ የምንባላበት አይደለም" ሲሉ የግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊቀመንበር አስገነዘቡ።

ሊቀመንበሩ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ባለፈው ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን በአምስተርዳም ከተማ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ባደረጉት ውይይት በቋፍና በጣዕረ-ሞት ላይ የሚገኘውን የመለስ አገዛዝ ከስሩ ለመንቀል እየተደረገ ባለው ዘርፈ-ብዙና ሁለ-ገብ ትግል ኢትዮጵያውያኑ ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጎን በመቆም እያደረጉት ላለው ተሳትፎ አድናቆታቸውን በመግለፅ፣ "በምንም ዓይነት መንገድ እርስ በርሳችን በመዘላለፍ የምናገኘው ጥቅም ስለሌለ፣ ለዚህ አይነቱ ፖለቲካ የምናባክነው ጊዜ የለም፤ ወቅቱ በጋራ እና በእልህ ተነስተን ነፃነታችንን የምናረጋግጥበትና አገራችንን የምንታደግበት ነው" ብለዋል።

በውጭ አገር የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን "ተሰባስበን ፖለቲካን እንደ መደበሪያ የምናወራበት ጊዜ አብቅቷል፤ ከስራ ደክሞን ወደ ቤት ስንመጣ ኮምፒውተር ላይ ተለጥፈን ሌላውን የምናንቋሽሽበት የመዘላለፍ ፖለቲካ አብቅቷል" ያሉት ዶክተር ብርሀኑ፤ "ከአሁን በሁዋላ በወያኔ ምንነት ላይ የሚደረግ ባዶ ክርክር ዋጋ የለውም። ስለ ወያኔ ማንነትና ክፋት ከበቂ በላይ አውቀናል። ያንን ደጋግሞ የሚነግረን ሰው አንፈልግም፤ የምንፈልገው ተግባር ብቻ ነው" ሲሉ በሁሉም ዘርፍ የሚደረግን የተግባራዊ ተሳትፎ አስፈላጊነት በአፅንኦት አስገንዝበዋል።

እንደ ዶክተር ብርሀኑ ገለፃ ወላጆች ለልጆቻቸው ከሚያወርሷቸው ሀብቶችና ንብረቶች መካከል መተኪያ ሊገኝለት የማይችለው ታላቅ ሀብት ነፃነት ነው። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በረከት ስምዖን የወያነን ገሀድ የወጣ ገበና ፤በብዕር ስም ለማስተባበል ሞከረ

በረከት ስምኦን ዛዲግ አብርሃ በሚል የብዕር ስም ወያኔ የብአዴን አባላትን ከመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ የማጽዳት አላማ እንደሌለው፣ ይልቁንም የህወሓትና የብአዴን ጥምረት በአላማ ቁርኝት ላይ የተመሰረተ ነው በማለት ለማስተባበል መሞከሩ ተጋለጠ።

በፍርሃት ተጠምዶ የሰነበተው ወያኔ፥ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የዘር ማጽዳት ስራ እየሰራ መሆኑን መካዱን ተያይዞታል። ሰሞኑን በወያኔ ፕሮፓጋንዳ አውታሮች በሚወጡ መልእክቶች የብአዴን አባላትን በማባበል እና በማሞኘት በድርጅታዊ አንድነት ስም የወያኔ ባርነታቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ሙከራ እያደረገ መሆኑ ታወቀ።

ወያኔ፥ መንግስቴን ሊገለብጡብኝ ሲሉ ያዝኳቸው ብሎ ከአርባ በላይ በብሔር አማራ የሆኑ የመከላከያ አባላትንና ሲቪል ዜጎችን ሰብስቦ ካሰረ በኋላ፣ በተለይ በመከላከያው ውስጥ የዘር ማጽዳት ዘመቻውን እንዳባባሰው ደጋግመን ማጋለጣችን ይታወሳል። የውስጥ አዋቂ ምንጮችንም ጠቅሰን በየቦታው በርካታ የቀድሞ እና ነባር የብአዴን አባላት፤ እንዲሁም ሌሎች የአማራ ብሔር አባላት እየታደኑ በመታሰር ላይ እንደሚገኙ፤ የተቀሩትም ቤተሰብ እና ቀዬያቸውን እየጣሉ ለስደት መዳረጋቸውን መዘገባችን ይታወሳል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ወታደራዊ እርዳታ የሚከለክለው የ አሜሪካ ህግ ለመለስ አገዛዝ የመጨረሻው መጀመሪያ ሆኗል።

የፖለቲካ ሳይንስ መምህር፣ ጠበቃ እና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ለሚደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋጾ በማድረግ ከሚታወቁት የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያን አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማሪያም ትናንት ሰኞ እለት ለድረ-ገጾች ባሰራጩት ጽሁፍ፣ ፕሬዘዳንት በራክ ኦባማ በግንቦት ወር የፈረሙት እና ኤች.አር 1105 በመባል የሚታወቀው ህግ፣ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ወያኔን ሲያውረጠርጡት ከነበሩት ነገሮች አንዱ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለፃ፥ ይህ ህግ በተከታታይ በህዝቦቻቸው ላይ ግፍ ለሚፈጽሙ አምባገነን መንግስታት ወታደራዊ እርዳታ እንዳይሰጥ የሚከለክል ሲሆን፣ ኢትዮጵያንም ከነዚሁ ሀገራት ተራ ሰይሟል። በተጨማሪም፥ ህጉ የአሜሪካ ፕሬዚደንት በሆነ ምክንያት ለኢትዮጵያ ወይም በዚህ ህግ ለተሰየሙት ሌሎች ሃገሮች ወታደራዊ እርዳታ መስጠት ቢፈልግ፣ ለህግ አውጪው አካል የበጀት ኮሚቴ ማስታወቅ እና ዝርዝር ምክንያቱንም ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ ጥገናዊ ለውጥ ለማድረግ ከጦር መኮንኖቹ ጋር ተመካከረ

የግንቦት 7 ንቅናቄ ባለፈው ሳምንት ለህዝብ ይፋ ባደረገው የመከላከያ ሰራዊት የአዛዦች ስም ዝርዝር ውስጥ ከህብረተሰባችን 6 በመቶ ብቻ የብሄረሰብ ተዋጽኦ ያለው ትግራይ ከ93 በመቶ በላይ የሆነውን የስልጣን እርከን መቆጣጠር በመቻሉ ከፍተኛ ህዝባዊ ቁጣ እየቀሰቀሰ ባለበት በዚህን ወቅት ህዝቡን ሊያረጋጋልኝ ይችላል ብሎ የሚያስበውን ጥገናዊ ለውጥ ለማድረግ የወያኔ አመራር እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘ መረጃ አጋልጦአል ።

ወያኔ ህዝቡን ያረጋጋልኝ ይችላል ብሎ ከሚያስባቸው ጥገናዊ ለውጦች ውስጥ እስከዛሬ ምንም የአዛዥነት ስልጣን ሳይኖራቸው የሌ/ጀነራልነት ማዕረግ ተሸክመው ለማዕረጉ የሚመጠን ደሞዝ ሲያገኙ የኖሩትን 5 የኦሮሞ ጀነራሎች በስልጣን ላይ ባሉ አዛዦች ፈንታ መተካት እንደታሰበ ፍንጭ ያለ መሆኑ ሲታወቅ፣ አሁን ካሉት የትግራይ ከፍተኛ መኮንኖች እነማንን ለመቀነስ እንደሚቻል ግን ግራ እንደተጋቡ ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአማራ ህዝብ ቁጥር ቀድሞ ከተገመተው በ2.7 ሚሊዮን አንሶ መገኘቱ ምንም ስህተት የለበትም ተባለ

ኮሚሽኑ ከአምስት ወራት በፊት የህዝብ ቆጠራ ውጤቱን ይፋ ባደረገበት ወቅት የአማራ ህዝብ ቁጥር 17 ሚሊዮን ብቻ ነው መባሉ አወዛጋቢ ሆኖ መገኘቱን እና በወያኔ ፓርላማ ውስጥ አንድም ነገር ተቃውመው የማያቁትን አንዳንድ የብአዴን አባላት ጭምር ማናደዱ ይታወሳል። የኢትዮጵያ ማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እራሱ ከሶስት አመታት በፊት የአማራን ህዝብ ቁጥር በግምት 19.7 ሚሊዮን እንደሆነ ማስቀመጡ እና ይህም በብዙ ባለሙያዎች ዘንድ ተቀባይነት እንደነበረው ይታወሳል።

አዲሱ የቆጠራ ውጤት ይፋ በተደረገበት ወቅትም ቁጥሩ በዛን ያህል አንሶ መገኘቱ ተቃውሞ ስላስነሳ በአዲሱ ለገሰ የሚመራው ኮሚሽን በጉዳዩ ላይ ምርመራ አድርጎ እንደሚመለስ መናገሩ ይታወሳል። ግንቦት 7 ቀን፣ 2001 አመተ ምህረት ኮሚሽኑ ለአምስት ወራት አድርጌዋለሁ በሚለው ምርመራ ላይ በመመስረት የህዝብ ቆጠራው ውጤት ትክክለኛ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ተዘግቧል።

ከአማራ ህዝብ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ህዝብ ቁጥር ከተገመተው እጅግ አንሶ መገኘቱ ብዙዎችን ያነጋገረ ጉዳይ እንደነበር ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። የአማራ እና የአዲስ አበባ ህዝብ በ97ቱ ምርጫ ቅንጅትን በብዛት በመምረጣቸው ለብዙ የወያኔ የበቀል እርምጃዎች ተጋልጠው መቆየታቸው ይታወቃል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ድጋፍ በግፍ ለታሰሩ ወገኖቻችን ቤተሰቦች

ወያኔ በመጀመሪያ መንግሥቴን ለመገልበጥ ሲያሴሩ ደርሼባቸዋለሁ ካለ በኋላ፤ ቆይቶ ደግሞ የለም ባለስልጣኖችን ሊገሉና ተቋማትን ሊያወድሙ ሲሉ ነው የደረስኩባቸው በማለት በርካታ ንፁሃን ዜጎችን ካሰረ አንድ ወር ሆነው፡፡ «አድመኞቹ ሲያደርጉት የነበረውን ሁሉ ከጥንስሱ ጀምሮ ስከታተል ስለነበር ስለ ሴራቸዉ ዝርዝር ማስረጃዎች አሉኝ፤ እመኑኝ ይኸው የማረኩሁት መሣሪያ፣ እቅድና ገንዘብ» በማለት የወረቀት ክምሮችን፣ የጦርመሣሪዎችን፣ የኤክትሮኒክስ እቃዎችን እና የብዙ አገራት የገንዘብ ኖቶችን በቴሌቪዝን ያሳየን ቢሆንም እስከዛሬ ድረስ ክስ አልተመሰረተባቸውም፡፡ እንዲያውም ክሱ ምን ተብሎ እንደሚመሰርትባቸው ገና ውሳኔ ያገኘም አይመስልም፡፡ ተገኘ የተባለው መረጃም በቅንጅት ጊዜ እንደቀረቡት መረጃ ተብዬዎች ሁሉ አድማጩን እንዳያሸማቅቁ በመፈራቱ የተጨማሪ መረጃዎች ፍብረካ እየተካሄደ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በከፍተኛ ሙቀት የተወራለት «የመጀሪያው የወያኔ የመፈቅለ መንግሥት ሙከራ» ክስ መጓተቱ የክሱ ዓይነት ለሶስተኛ ጊዜ ለመለወጥ ታስቦ፤ አሊያም በርከት ያሉ ሰዎችን ካሰሩ በኋላ የጅምላ ፍርድ በመስጠት የፍርድ ቤት ተብየውን ጊዜ ለመቆጠብ ታቅዶ ሊሆን ይችላል፡፡

ወያኔ የክሱን ዓይነት እየቀያረ ሊዘባርቅ ይችላል፡፡ ለኛ የሚያሳስበን ግን የክሱ ዓይነት ሳይሆን የወገኖቻችን እስር ጠንክሮ መቀጠሉ፣ በእስረኞች አያያዝ ላይ የሚደርሱን አሳዛኝ ዘገባዎች እና በቤተሰቦቻቸው እየደረሱ ያሉ ችግሮች ናቸው፡፡

ወያኔ ለነፃነቱ ቀናኒ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያለውን ጥላቻ በመዳፉ ውስጥ በሚገኙት እስረኞች ላይ አያያዝ ላይ እያሳየው ነው፡፡ በደርሱን መረጃዎች መሠረት እስረኞቹ ላይ የተለያዩ አካላዊና ስነልቦናዊ ስቃይ እየደረሰባቸዉ ነው፡፡ በእድሜ የገፉትና የጤና እክል ያለባቸው እንኳን ሳይቀሩ ተደብድበዋል፤ በወያኔ ፖሊሶችና ሰላዮች ተተፍቶባቸዋል፡፡

በእስረኞቹ ላይ የሚደርሰው ጥቃት ለመሸፈን እስከዛሬ ድረስ በቤተሰቦቻቸው፣ በጠበቆቻቸውና በጤና ባለሙያዎች እንዳይጎበኙ የተከለከለ ሲሆን፤ ወደ «ፍርድ ቤት» ተብዮው የአሳሪዎቹ ሌላ ቢሮ ሲጓጓዙም እንዳይታዩ የሚደረገው መሸፋፈን እኛ የለመድነው ቢሆንን ባዕዳንን ግን በእጅጉ አስገርሟል፡፡

«የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ የውሸት ፋብሪካው የሆነው የወያኔው አፈቀላጤ «ጠያቂ ስለሌላቸው ነው እንጂ እኛ የእስረኞቹን ጉብኝት አልከለከልንም» በማለት በተበዳይ ዘመዶችና በመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተሳልቋል፡፡ ይህ ስላቅ ሁላችንምም አሳምሟል፡፡ እውን እነዚህ የዘረኝኛና አምባገነን ግንባር ሥርዓት ሰለባዎች ናቸው ጠያቂ የማይኖራቸው?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔ ሰለባዎች ያለውን አጋርነት በተለያዩ መንገዶች ሲገልፅ ቆይቷል፡፡ የቅንጅት መሪዎች በታሰሩበት ወቅትም ሆነ አሁን በወ/ት ብርተካን ሚደቅሳና እና ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን እስር ጉዳይ ላይ እየታየ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሰላማዊ ሰልፎችና የሻማ መብራቶችን ከማድረግ አልፎ የእስረኞቹን ቤተሰቦች በመደገፍ ረገድ ያደረጉት መረባረብ በጭራሽ የሚረሳ አይደለም፡፡

አሁን ደግሞ ተመሳሳይ እርምጃዎች በተጠናከረና በተደራጀ መንገድ ከመንግስት ግልበጣ ክስ ጋር በተያያዘ ለታሰሩትም መደረግ እንዳለበት ማሳሰሰብ እንወዳለን፡፡

የወያኔ ተቃዋሚዎች በመሆናቸዉ ብቻ የመንግሥት ግልበጣ ታሪክ ተፈብርኮላቸዉ ለአስከፊ እስርና ሰቆቃ የተጋለጡ ወገኖቻችን ጉዳይ እንደ አንድ መሠረታዊ አጀንዳ መያዝ ይኖርብናል እንላለን፡፡ ብዙዎች በእድሜ የገፉ አዛውንትና የበርካታ ቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በመሆናቸው ለቤተሰቦቻቸው ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ስለሆነም እስረኞችን ለማስፈታት የሚደረጉ ትግሎችና ለቤተሶቻቸውም የሚደረገው ድጋፍ በተደራጀና በተጠናከረ መንገድ መቀጠል እንዳለበት አበክረን ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

## ወያኔ የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ ጥገናዊ ለውጥ ለማድረግ ከጦር መኮንኖቹ ጋር ተመካከረ (ከገጽ 1 የዞረ

በዚህም የተነሳ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ሳሞራ የኑስና ሌሎች ለርሱ የሚቀርቡ ከፍተኛ የጦር አዛዦችን አስጠርቶ እንዳወያየና ከስልጣናቸው በገዛ ፈቃዳቸው ለመነሳት ለሚስማሙ አዛዦች በሥራ ላይ ባሉበት ወቅት የሚከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች እንደማይነካባቸው፤ እንዲያውም ዳጎስ ያለ ገንዘብ በካሳ መልክ እንደሚከፈላቸው በሚስጥር ለእያንዳንዱ ባለከፍተኛ ማዕረግ እንዲነገራቸው ስምምነት እንደተደረገ ታውቋል። በተጨማሪም ለሞራላቸው መጠበቂያና ለማበረታታቸነት በአማካሪነት ወይም በኤክስፐርትነት ደረጃ በሰራዊቱ ውስጥ እንዲቆዩ እንደሚደረግ ሃሳብ አንዳለ ለማወቅ ተችሎአል ።

የዜና ምንጮቻችን በአደረሱን በዚህ መረጃ መሰረት አብዛኛው የጦር አዛዥ በሰራዊቱ ወስጥ እየተጠናከረ በመጣው ተቃውሞና የሙብት ጥያቄ ትልቅ ስጋት እየገባው በመሆኑ፤ አስከዛሬ ምንም የአዛዥነት ልምድ እንዲያዳብሩ ያልተደረጉ የማእረግ አቻዎቻቸው በቀላሉ ሊፈነዳ ለሚችለው ለዚህ ተቃውሞ መፍትሄ ሊሰጡ ይችላሉ የሚል እምነት እንደሌላቸው ስጋታቸውን ሳይደብቁ ለአለቃቸው ለመለስ ዜናዊ በውይይቱ ወቅት እንደተናገሩ በዚህም የተነሳ መለስ እራሱ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ እንደተዘፈቀ የተገኘው መረጃ ያስረዳል ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የግንቦት 7 ንቅናቄ ዲፕሎማሲ ቡድን ሰሞኑን ያነጋገራቸው አንዳንድ የምዕራብ አገር መንግስታት ባላስልጣኖችና ወኪሎች ግንቦት 7 ይፋ ባደረገው፣ በዚህ የአንድ ብሄረሰብ አባላት መከላከያ ሰራዊቱን የመቆጣጠር ዜና፣ እጅግ እንደተገረሙና የመለስ አገዛዝ እንዲህ ዓይነት ዘረኛ አመዳደብ በጦሩ ውስጥ ያሰፍናል ብለው በፍጹም አስበው ወይም ጠብቀው እንደማያውቁና አይናቸውን ማመን እንዳቃታቸው ሳይሸሽጉ መናገራቸውን ለዝግጅት ክፍላችን በተላከው ዜና ለማወቅ ተችሏል። ዜጎች ሁሉ በእኩልነት ሊስተናገዱበትና በዘር ትስስር ወይም በፖለቲካ ታማኝነት ሳይሆን በችሎታ ብቃት መመዘኛ መዋቀር ባለበት የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ እንዲህ አይነት ያገጠጠ ዘረኝነት ከሰፈነ በሌሎች የመንግሥት ተቋማትና የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ሊኖር የሚችለውን በምንም መስፈርት ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል ዘረኛ አድሎ መገመት አያስቸግርም ያሉት እነዚህ ምዕራባውያን፤ የቡሽ ጸረ-ሽብርተኝነት ፖሊሲ በከፈተው ቀዳዳ መለስ ዜናዊ በድህረ ምርጫ 97 በገዛ አገሩ ህዝብ ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ አለም አቀፍ ትኩረት እንዳይኖረው መደረጉ በ21ኛው ክፍለዘመን የተፈጠረ አንድ አቢይ ስህተት ነው ብለዋል።

ግንቦት 7 ንቅናቄ በፖሊስ ሰራዊት፣ በደህንነትና በፍትህ አካላቱ ውስጥ ያለውን የሰው ሃይል አመዳደብ በብሄረሰብ ተዋጽኦዋቸው ዝርዝሩን ለህዝብ ይፋ የማድረግ ዕቅድ እንዳለው ሲታወቅ፣ ላለፉት 18 ዓመታት የአገሪቱን አንጡራ ሃብት ለመመዝበር በትላልቅ የኢኮኖሚ ተቋሞች ላይ ተመድበው ወንጀል እየፈጸሙ ያሉትን ሁሉ ለማጋለጥ እንዲቻል ህብረተሰቡ በእጁ ያለውንና የሚያውቀውን መረጃ ሳይንቅ ለንቅናቄያችን ህዝብ ግንኙነት በኢሜል ወይም በደብዳቤ እንዲገልጽ የግንቦት 7 ንቅናቄ ህዝባዊ ጥሪ አቅርቧል።

## ወታደራዊ እርዳታ የሚከለክለው የ አሜሪካ ህግ ለመለስ አገዛዝ የመጨረሻው ......(ከገጽ 1 የዞረ

የኦባማ አስተዳደር በዚህ ህግ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ገዢዎች እያስተላለፈ ያለው መልእክት ግልጽ ነው የሚሉት ፕሮፌሰር፤ “አሜሪካ ሲቪሉን ህዝባችሁን የሚያሸብሩትን ወታደሮች ታሰለጥኑ ዘንድ አምስት ሳንቲም አትሰጣችሁም፤ ወይም ጦሩ ህዝቡን ይገልበት ዘንድ አንድም ጠብ መንጃ፣ አውሮፕላን፣ ታንክ ወይም መኪና አትሰጥም።” ማለቷ ነው ብለዋል።

ፕሮፌሰር አለማየሁ ጨምረውም፥ ከሚከለከለው እርዳታ ይልቅ በዚህ ህግ ማለፍ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ፣ የኢትዮጵያው አገዛዝ ህዝቡን ለማፈን እና መብቱን ለመጣስ የአሜሪካንን ወታደራዊ እርዳታ በመጠቀሙ ላይ የሚያስተላልፈው የተሸፈነ ውግዘት ነው ብለዋል።

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 55 ግንቦት 27, 2001 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# የኢትዮጵያ የደህነት ችግሮችና መፍትሄ

## 1. መግቢያ

የሶማሊያ የባህር ላይ ጠላፊዎች ተግባርና የዳርፉር ሰቆቃ እረፍት የነሳቸዉ የአሜሪካ ወይም የአዉሮፓ ፓለቲከኞች ኢትዮጵያን በሰላም ደሴት ቢመስሏት ብዙም አይገርምም፡፡ እንኳንስ እነሱና በሩቅ ሆነው ሰዎችን መዘዋወራቸውን፤ ተማሪዎች ት/ቤት ገብተው መውጣቸውን፤ የእምነት ቦታዎች የዘወትር ተግባራቸውን ማከናወናቸውን ያስተዋለ የዋህ ኢትዮጵያዊም አገሪቱ በርግጥም የተረጋጋች ልትመስለው ትችላለች፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ ደግሞ ያለመታከት «የኢትዮጵያን ህዳሴ» ያበስራሉ፡፡ ውስጡን በጥንቃቄ ላጠና ግን ሁኔታው ከዚህ በጣም የተለየ ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታ በአየር የተነፋ ፊኛን ይመስላል፡፡ በአየር የተነፋ ፊኛ ያምራል፣ ያጓጓል፣ ቋሚ ነገርም ይመስላል፡፡ ሆኖም ፊኛው ይበልጥ ከተነፋ ወይም አንዳች ሹል ነገር ከነካው ፈንድቶ እንዳልነበር ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ደህንነት በቅራኔዎች ተወጥሯል፤ አሁንም በቅራኔዎች ይበልጥ እየተነፋ ነው፡፡ በፊኛው ዙርያ በርካታ ሹል ምስማሮችና እሾሆች አሉ፡፡ አደጋው ቅርብና በጣም አሳሳቢ ነው፡፡

## 2. አቢይ የደህንነት ችግሮች

የኢትዮጵያን ዋና ዋና የደህንነት ችግሮች ውስጣዊና ውጫዊ ብለን በሁለት ከፍለን ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡

### 2.1 ዉስጣዊ የደህንነት ችግሮች

#### 2.1.1 ድህነትና ኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል

አንዱ የሃገራችን የደህንነት ችግር ምንጭ ድህነት ነው፡፡ ይህንን ወያኔም አዘዉትሮ ይናገራል፡፡ ድህነት በውግዘት የሚጠፋ ቢሆን ኖሮ ወያኔ ድህነትን ከመላው አፍሪቃ ባስወገደ ነበር፡፡ ሃቁ ግን የወያኔ የኢኮኖሚ ፓሊዎች ድህነትን ማብዛታቸው ነው፡፡ የዘመኑ ወያኔ ድህነት እጅግ አደገኛ የሆነ ነገር ጨምሮ ይዞ መጥቷል - ግልጽ የሆነ ኢፍትሃዊ የሃብት መበላለጥ፡፡ የወያኔ የኢኮኖሚ ፓሊሲዎች ብዙዎችን ሲያደኸዩ በጣም ጥቂቶችን ግን ሰማይ ጥግ አድርሷቸዋል፡፡ በጣም አስደንጋጭ የሚሆነው ደግሞ እነዚህ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎችን በሃብት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ማህበራዊ መለኪያዎች የሚለዩ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በሃብት ክፍፍሉ ሰበብ የሚነሳ ቅራኔ በፍጥነትና በቀላሉ ወደ ዘውግ እና ፖለቲካ አመለካከት ሊያመራ ይችላል፡፡ እናም ቅራኔው በጥቂት ሃብታሞችና በብዙሃን ድሆች መካከል ያለ ቅራኔ ሆኖ ላይዘልቅ ይችላል፡፡

#### 2.1.2 ዘውግን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች መበራከት

በሃገራችን በሚገኙ ዘውጌ ማህበረሰቦች (ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ ሕዝቦች) መካከል የሚነሱት ግጭቶች ቁጥር እና በህይወትና ንብረት ላይ የሚያደርሱት ጉዳት በከፍተኛ መጠን ጨምሯል፡፡ አገሪቷ በመላ እዚህም እዚያም በሚፈነዳዱ የብሄር፣ ብሄረሰብ ግጭቶች ተሞልታለች፡፡ የችግሩን ስር መስደድ ለማጤን ዩኒቨርስቲዎችን መመልከት ይበቃል፡፡ ለምሳሌ በጅማ ዩኒቨርስቱ አንድ የትግራይ ተማሪ ቢደበደብ፤ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ያሉ የትግራይ ተማሪዎች አጠገባቸው ባሉ የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ የበቀል እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ በሃረማያ ዩኒቨርስቲ ያሉ የኦሮሞ ተማሪዎች ደግሞ አጠገባቸዉ ባሉ የትግራይ ተማሪዎች ላይ የአፀፋ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ እንዲህ እያለ አገሪቷን ያዳርሳታል፡፡ ሁኔታውን አጤኖ ላየው ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የተከላቸው ጥላቻዎች የጠበቀውን ያህል ባይሆንም ፍሬ አፍርተዋል፤ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ፍሬዎቹ በስለዋል:: የኦጋዴንና የጋምቤላ ጉዳዩች በዓለም ዓቀፍ መድረኮች መነሳት ከጀመሩ ሰንብቷል፡፡ በሌሎችም አካባቢዎች አስከፊ ግጭቶች ለመፈንዳት ሁኔታዎች ተመቻችተው ትንሽ ሰበብ ብቻ የሚጠብቁ ይመስላል፡፡

#### 2.1.3 የሃይማኖች ግጭቶች መበራከት

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚያስፈራ ሁኔታ እየተባባሰ ያለው በተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ያለዉ መፋጠጥ ነው፡፡ በእስልምናና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ፤ በኦርቶዶክስ ተዋህዶና በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መካከል ያለው ቅራኔ ወደ አደባባይ የወጣበት አስጊ ደረጃ ላይ እንገኛለን፡፡ የሃይማኖት አባቶች የሌሎች ሃይኖቶች ነቢያትን ሲዘልፉ መስማት፤ በእምነት ቦታዎች ግጭቶች መብዛታቸውን ስናስተዉል ማህበረሰባችን የተገነባበት መሠረት እየተናደ እንደሆነ ይሰማናል፡፡ እንደሚታወቀዉ የሃይማኖት ግጭቶች ከተነሱ በቀላሉ የማይበርዱ ከመሆናቸውም በላይ በቀላሉ ድንበር ተሻጋሪዎች ናቸው፡፡

#### 2.1.4 የተቋማት የሕዝብ አመኔታ ማጣት

ሌላዉ አሳሳቢ ጉዳይ የዜጎች በተቋማት ላይ እምነት ማጣት ነው፡፡ ከፓርላማው ቁምነገር ይገኛል ብለው እንኳንስ ዜጎች ራሳቸው የፓርላማው አባላትም አያምኑም፡፡ የመከላከያ ሠራዊት እና ፓሊስ በመከታነት መታየታቸው ቀርቶ መንግሥት ሕዝብን የሚያጠቃበት መሣሪያ በመሆናቸው የሚፈሩና የሚጠሉ ሆነዋል፡፡ «ፌደራል ፓሊስ»፣ «አግዓዚ» የሚሉ ቃላት እንኳንስ ህፃናትን አዋቂዎችንም ያስበረግጋሉ፡፡ የአገሪቱ የስለላ ተቋም «ጆሮ ጠቢ» ነው የሚባለው፡፡ ምርጫና ፍርድ ቤቶች መቀለጃ ሆነዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮን «በተቃራኒ መስማት» በጣም ተለምዷል፡፡ አድማጮች እውነታው ከተነበበው ዜና ተቃራኒ ሊሆን እንደሚችል ከመጠርጠር አልፈው ማመን ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ የሃይማኖት ተቋማትም ተዓማኒነታቸው እጅግ ወርዷል፡፡ ኢትዮጵያ አንዱ ጳጳስ ሌላኛዉን ጳጳስ በቴሌቪዥን ቀርቦ ሲያወግዝ የተሰማባት አገር ሆናለች፡፡ በፓለቲካ ፓርቲዎች ላይ ያለው እምነትም በእጅጉ ተሸርሽሮዓል፡፡ ወያኔን መደገፍ ለጥቅም፤ ተቃዋሚዎችን መደገፍ ደግሞ ጊዜ ማሳለፊያ እየሆነ ነው፡፡ የእምነት መሸርሸር በዘወትር ህይወት ውስጥ የሚታይ ክስተት ሆኗል፡፡ ከበርበሬ ጋር አፈር፤ ከቅቤ ጋር ሙዝ ቀላቅሎ መሸጥ ብልጠት እንጂ አስነዋሪ ነገር አይደለም፡፡ እንዴት ነው በዚህ ሁኔታ መንግሥት እያስተዳደርኩ ነው ሊል የሚችለው?

### 2.2 ዉጫዊ የደህንነት ችግሮች

#### 2.2.1 ኤርትራ

የወያኔን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ካጋለጡ ነገሮች የኤርትራን ጉዳይ የመሰለ ያለ አይመስልም፡፡ መጀመሪያ ለኤርትራ ጉዳይ ከሁለቱም ውንድማማች ህዝብ ጋር በመመካከር ፖለቲካዊ መፍትህ እንዳይበጅ በማድረግ በሁለቱ ህዝብ መካከል ለዘመናት የሚቆይ ጥላቻን እና ጦርነት ሊፈጢር የሚቹል አደጋ የሚጋርጥ ውሳኔ በማድረግ ሁለቱን አገሮች በማለያየት ወንጀል ስራ። ቀጥሎ በቂ ምክንያት ሳይኖር ወደ ጦርነት ገብቶ ከዚያም የተስማማበትን የአልጀርስ ስምምነት በመጣስ የሄው ችግሩ ተፈትቷል አለን። ከኤርትራ ጋር ያለው ውጥረት አለመርገቡ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ሰላም ደንቃራ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

#### 2.2.2 ሶማሊያ

ወያኔ ሶማሊያ ውስጥ የገባበት ማጥ ዩስ አሜሪካ በኢራቅ ከገባችበቱ ይብሳል፡፡ የሶማሊያ የውስጥ ችግር ኢትዮጵያ ለመድረስ ወንዝ መሻገርም ሆነ አስተርጓሚ መፈለግ አያሻውም፡፡ ወያኔ ሶማሊያን በመዉረሩ ኢትዮጵያን በእጅጉ ጎድቷል፡፡ ሶማሊያውያን ፓለቲከኞች ከወረራው በፊት ከነበሩት ይበልጥ ጽንፈኛ አቋም ይዘዋል፤ ከወረራው በፊት ከነበረው ብዙ ጊዜ እጥፍ የላቀ በኢትዮጵያ ላይ ቂም ቋጥረዋል፡፡ ወያኔ ሶማሊያ ውስጥ የፈጠረው ቀውስ መዘዝ ለብዙ ጊዜ አብሮን መቆየቱ አይቀርም፡፡

#### 2.2.3 ሱዳን

ከሱዳን ጋር ሞቅ ቀዝቀዝ የሚለው ግኑኝነት ወደየት እንደሚያመራ መገመት ከባድ ነው፡፡ በተለይም የደቡብ ሱዳን ዉሳኔ-ህዝብ ሉዓላዊት አገር በመፍጠር የሚጠናቀቅ ከሆነ በአፍረቃ ቀንድ አዲስ ጂኦ-ፓለቲካ ይፈጠራል፡፡ የደቡብ ሱዳን መገንጠል ደግሞ በተቀረው ሱዳን ላይም ጫና ይኖረዋል፡፡ ወያኔ ይኸንና በዚያ በኩል ሊመጣበት የሚችለዉን ጥቃት ለማክሸፍ አስቦ ሊሆን ይችላል መሬት በመስጠት ወዳጅነትን የማጠንከር ፓሊሲን የሚያራምደው፡፡ አሁን ደግሞ መለስ እና አል-በሽር የዓለም ዓቀፉን የወንጀለኞች ፍርድ ቤትን በማውገዝ አጋርነታቸው ጠንክሯል («ጓድ» ቢባባሉም ያምርባቸዋል)፡፡ የሱዳንን መንግሥት ለማስደሰት ያደረገዉ ግልፅነት የጎደለው የመሬት ስጦታ ከሱዳን ጋር የረዥም ጊዜ ችግር ሊፈጥርብን ይችላል፡፡

#### 2.2.3 ጂቡቲ

ጂቡቲ ለኢትዮጵያ ደህነት ያላት ሚና ከትላልቆቹ አገሮች ቢበልጥ እንጂ አያንስም፡፡ ጂቡቲ ኢትዮጵያን ማጥቃት ብትፈልግ የየብስ፣ የአየርና የባህር ክልሏል ለኢትዮጵያ ጥቅም እንዳይሰጡ በማድረግ ብቻ ኢትዮጵያን ማስጨነቅ ትችላለች፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር ፈፅሞ ሊፈጠር አይችልም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ጂቡቲ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያዊያን ሾፌሮች የሚማረሩባት አገር ናት፡፡ የጂቡቲ መንግሥት ከወያኔ ጋር ቅርበት ያለው ቢሆንም በሶማሊያ ውስጥ በፈጠረው ትርምስ ሳቢያ የጂቡቲ ዜጎች በእጅጉ አለመደሰታቸው ይሰማል፡፡

#### 2.2.4 ሌሎች የአካባቢው አገሮች

የወያኔ የዉጭ ጉዳይ ፓሊሲ ከሌሎች የአካባቢው አገሮች ጋር ያለው ግኑኝነት የቀዘቀዘ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ኢትዮጵያ ከግብፅ ጋር ያላት የዲፕሎማሲ ግኑኝነት የይስሙላ የሚባል ዓይነት ነው፡፡ ከአረብ ሰላጤ በተለይም ከኳታር ጋር ያለው ግኑኝነት እጅግ የቀዘቀዘ እና በጥርጣሬ የተሞላ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ለም መሬት በርካሽ የሚገኝባት በመሆኗ የአካባቢው ቱጃሮች የድርሻቸውን ለመዉሰድ ዝግጁ ናቸው፡፡ በርካታ የእርሻ መሬት ለአረብ ቱዳሮች መስጠት የረዥም ጊዜ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል አሁን በርጋታ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ **ይቀጥላል**

## ልዩነቶቻችን አቻችለን በእልህና በጋራ አገራችን ለማዳን የምንነሳበት ጊዜ አሁን ነው (ከገጽ 1 የዞረ)

በስብሰባው የተገኙት ኢትዮጵያውያን በበኩላቸው፣ ወቅቱ ለሚጠይቀው ሁለንተናዊ ትግል ከንቅናቄው ጎን በመቆም እንደ ችሎታቸውና እንደ አቅማቸው አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ የአምስተርዳም ዘጋቢ ከስፍራው ከላከልን ዘገባ መረዳት እንደተቻለው፣ ንቅናቄው ባለፈው ቅዳሜ ያካሄደው ይህ ስብሰባ፣ ባለፉት ዓመታት በአምስተርዳም ከተማ በኢትዮጵያውያኑ ተደርገው ከነበሩት በርካታ ስብሰባዎች እጅግ ደማቅና ብዛት ያለው ሰው የተገኘበት ሲሆን፤ በስብሰባው ፍጻሜ ንቅናቄው ለጀመረው ትግል ማጠናከሪያ ይውል ዘንድ ገንዘብ መዋጣቱም ታውቆአል።

በማግስቱ ዕሁድ ጠዋት ለተመሳሳይ ዓላማ ወደ እንግሊዝ በማምራት በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ በለንደን ከተማ በተደረገው ታላቅ ስብሰባ ላይ በመገኘት ስለንቅናቄያቸው ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በዚህ ስብሰባ ላይ ለኢትዮጵያውያን ባደረጉት ንግግር በኢህአዴግ የሚመራው አምባገናንዊ መንግስትና በኢትዮጵያ ህዝብ እና በአገሪቱ ሉኣላዊነት ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ፤ እንዲሁም ለረዥም ጊዜ ነቀርሳ ሆኖ ሊቆይ የሚችለው የዘረኝነት ስርዓቱ ከስሩ መገርሰስ ያለበት አሁኑኑ ነው ሲሉ አበክረው ተናግረዋል።

ከ2 ሳምንታት በፊት የአውሮፓ ጉብኝታቸውን በስዊድን አገር የጀመሩት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ፤ ኢትዮጵያዊያን በብዛት በሚኖሩባቸው ከተሞች ሰፊ ውይይት በማድረግ ለንቅናቄው ሁለገብ ትግል ማካሄጃ የገንዘብ ድጋፍ ከማሰባሰባቸውም በላይ ከየአገሩ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት ጋር በመገናኘት የግንቦት 7 ንቅናቄን አላማና የትግል ስትራቴጂ በሚገባ አስረድተው ባለፈው ማክሰኞ ወደ አሜሪካን አገር የተመለሱ መሆናቸው ይታውሳል።

## በረከት ስምኦን ወያኔ የብአዴን አባላትን ከመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ የማጽዳት አላማ የለውም ሲል የብዕር ስም በመጠቀም ለማስተባበል ሞከረ (ከገጽ 1 የዞረ)

በዚህ ጉዳይ ስጋት ሰቅዞ የያዘው ወያኔም ሰሞኑን የብአዴን አባላት እና የአማራ ህዝብ ህፃናት ይመስሉ ለማባበል እና ለማታለል የተለያዩ ጽሁፎችን እና ዝግጅቶችን በወያኔ የፕሮፓጋንዳ አውታሮች ላይ ማውጣት ጀምሯል። ባለፈው ሳምንት በበረከት ስምኦን ተጽፎ ዛዲግ አብርሃ በሚል ስም በወያኔ የዜና አገልፍሎት ድረ-ገጽ ላይ የተለጠፈ አንድ ጽሁፍም፣ የብአዴን እና የህወሓት ግንኙነት በመርህ እና በዓላማ አንድነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና ህወሓት በፍጹም ይህን አጋር ድርጅቱን ለማዳከም እንደማይሰራ በተለመደው የወያኔ "ኑና ላሞኛችሁ" ዘይቤ ዘርዝሯል።

የጎንደር ህዝብ በረከተ-መርገም ብሎ የሚጠራው የወያኔ አፈ ቀላጤ በዚህ ጽሁፍ ስለ ብአዴን እና ህወሓት ግንኙነት አይነኬነት ሊያስረዳ ሲሞክር፣ የሁለቱን ድርጅቶች ታሪካዊ መደጋገፍ፤ እንዲሁም የአማራን እና የትግራይን ህዝብ ወንድማማችነት ጠቅሷል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አንድ አስተያየት ሰጪ፥ "እርግጥ ነው ብአዴን ኢህዴን በነበረበት ወቅት ከወያኔ ጋ የአላማ አንድነት የነበረው መስሎት ጎን ለጎን ሆኖ ተዋግቷል። ወያኔ ስልጣኑን ከተቆጣጠረው በኋላ ግን ገና ጥቂት ሳይቆይ ነበር አብዛኞቹ የያኔው ኢህዴን አባላት እየተከሰተ ያለው ነገር የታገሉለት እንዳልሆነ በመናገር መቃወም የጀመሩት። ያ ተቃውሞ ፈንድቶ ያልወጣበት ብቸኛው ምክንያት በነተፈራ ዋልዋ መሪነት ሲደረግ ከቆየው አፈና የተነሳ ብቻ ነው። በረከት ይህንን ለምን ዘለለው?" ሲሉ ጠይቀዋል።

በቅርብ ጊዜ የወያኔ የቀድሞ ባለ ስልጣን እና ያሁን ስደተኛ ተስፋዬ ገብረአብ ባሳተመው መጽሃፉ ላይ "መዝሙረ ዋልዋ" በሚል ክፍል ተፈራ ዋልዋ እንዴት አድርጎ የብአዴን ታጋዮችን ቅስም በሚሰብሩ ስድቦች ተቃውሟቸውን ያፍን እንደነበር በዝርዝር መፃፉ ይታወቃል።

በረከት ስለሁለቱ ህዝቦች ወንድማማችነት የተናገረውን በተመለከተ የጠየቅናቸው አስተያየት ሰጪ፥ "እርግጥ ነው፤ ሁለቱ ህዝቦች ወንድማማቾች ናቸው፤ እሱ ከወያኔ በስተቀር የማንም ጥያቄ ሆኖ አያውቅም። እንደውም የኛ ጥያቄ ወያኔ ይህንን በሁለቱ ህዝቦች መሃል ያለውን ወንድማማችነት ብቻ ሳይሆን፣ በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ መሃል ያለውን ወንድማማችነት አሽቀንጥሮ ጥሎ አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች ብሎ ለምን ሾመ የሚለው ነው" ብለዋል። ጨምረውም፥ ወያኔ በአማራ ህዝብ ላይ የስድብ ውርጅብኝ ማውረድ የጀመረው ገና ጫካ እያለ እንደነበረ፤ እንዲሁም አንድ የፖለቲካ ችግር በገጠመው ቁጥር እየተነሳ የአማራን ህዝብ ትምክህተኛ እያለ በጅምላ መሳደብ የለመደው አሰራር መሆኑን አስታውሰው፣ በረከት በዚህ ጽሁፍ ማንን ሊያታልል እንደፈለገ እንዳልገባቸው ተናግርዋል። ከጥቂት ወራት በፊት አንድ የወያኔ የውስጥ አዋቂ መለስ ዜናዊ ከህወሃት ጓደኞቹ ጋር ሲሆን የብአዴን ባለስልጣናትን፣ "እነዚህ ከብአዴን በኮታ የወሰድናቸው አህዮች" እያለ እንደሚያንቋሽሽ ማጋለጣቸው ይታወሳል።

በረከት በጽሁፉ ህወሓት እና ብአዴን የትግል አጋሮች መሆናቸውን ደጋግሞ መግለጹን በተመለከተ ያነጋገርናቸው ሌላ አስተያየት ሰጪ፥ "እርግጥ ነው ህወሓት ጭንቅ በገጠመው ቁጥር ብአዴን የትግል አጋሩ እንደሆነ ደጋግሞ ይናገራል። እውነታው ግን፣ ህወሓት ገዢው ሲሆን ብአዴን ጉዳይ አስፈፃሚ አሽከሩ ብቻ ነው" ሲሉ ተናግረዋል። ለዚህም እንደማስረጃነት፣ በየጊዜው ህወሃት በኦህዴድ እና በብአዴን መሃል ቡድን እየቀያየረ አንዱን ሲመታ ሌላውን የሚጠቀምበትን አሰራር በመጥቀስ፣ "ይህ የሚደረገው ብአዴን መጠቀሚያ ብቻ ስለሆነ" ነው ብለዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ጦር ውስጥ ካሉት 61 ቁልፍ መቀመጫዎች ውስጥ ሁለት አማራዎች ብቻ እንዳሉ፣ እና ከ91 በመቶ በላይ የሚሆነው ቦታ በትግራይ ተወላጆች መያዙን ማጋለጡ ይታወሳል። በተጨማሪም፥ የፖሊስ፣ የደህንነት እና የሲቪል መስሪያ ቤቶች ቁልፍ ቦታዎች፤ እንዲሁም ኢኮኖሚው ከአንድ ዘውግ በተውጣጡ ሰዎች ቁጥጥር ስር እንደሚገኝ ከምንጊዜውም በላይ ለህዝቡ ግልጽ እየሆነ መጥቶአል።

ይህንን በአደባባይ አግጦ የወጣን ሃቅ ለመሸፋፈን በረከት በብእር ስም ካደረገው ሙከራ በተጨማሪ፥ አይጋ ፎረም በተባለው የወያኔ ድረ-ገጽ ላይ የቀድሞውን ኢህዴን ታጋይ ኮበሌን የሚያወድስ ግጥም የወጣ ሲሆን፤ ወያኔ በሚጫወትበት የኢትዮጵያ ቴለቪዥን ላይም በብአዴን እና በወያኔ መሃል ጠንካራ ግንኙነት እንዳለ አድርገው ለማሳየት የሚሞክሩ ዝግጅቶች እየቀረቡ እንደሆነ ታውቋል።

ያለ ፍላጎቱ ከጎንደር ተቆርጦ የትግራይ አካል እንዲሆን ከተደረገው እና የብዙ ግፍ ቀማሽ ከሆነው የወልቃይት ጸገዴ ህዝብ ጀምሮ፣ የአማራ ህዝብ በወያኔ የሚደርስበትን ግፍ መቃወም ከጀመረ አመታት እንዳለፉ የሚናገሩት አንድ አስተያየት ሰጪ፣ ይህ ሁሉ ተቃውሞ በነበረከት ስምኦን አፋኝነት ምክንያት እንዲዳፈን ሲደረግ መቆየቱን ገልጸዋል። "በረከት ስምኦን አሁን የብአዴን አባላት ህፃናት ይመስሉ በዚህ አይነት ጽሁፍ ኑ ላታላችሁ የሚለውም፣ ያ ሁሉ ተቃውሞ አሁን መፈንዳቱን እና መመለሻ እንደሌለው ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን፤ ለማንኛውም ለማሞኘት ልሞክር ብሎ ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

## የአማራ ህዝብ ቁጥር ቀድሞ ከተገመተው በ2.7 ሚሊዮን አንሶ መገኘቱ ምንም ስህተት የለበትም ( ከገጽ 1 የዞረ)

አገዛዙ ለክልሎች በጀት እና ለህዝብ ተወካዮች ተብዬው መቀመጫ የሚያከፋፍለው በየክልሎቹ የህዝብ ቁጥር ላይ ተመስርቶ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን የገለጹ ብዙ አስተያየት ሰጪዎች የአማራ እና የአዲስ አበባ ህዝቦች ቁጥር አንሶ መገኘት አገዛዙ ሆን ብሎ አይደግፉኝም ብሎ የሚያስባቸውን ህዝቦች ለመቅጣት እና ውክልና ለማሳጣት የሸረበው ሴራ እንደሆነ መናገራቸውን ከዚህ ቀደም ዘግበናል።

እንደተገመተውም፥ ከጥቂት ሳምንታት በፊት የወያኔ ፌዴርሽን ምክር ቤት ባጸደቀው የበጀት ቀመር የአማራ ክልል ድርሻ እንዲቀንስ መደረጉ ታውቋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪ፥ "ወያኔ በ97ቱ ምርጫ ክፉኛ በተጎዳባቸው አካባቢዎች ህዝቦች ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ ከጀመረ ቆይቷል። ብዙዎች ታስረዋል፣ ከስራ ተፈናቅለዋል፣ ተሰደዋል። የአማራን እና የአዲስ አበባን ህዝብ ቁጥር አሳንሶ ብቅ ማለቱም ገና ለገና የ97ቱ ውርደት ይደገምብኛል ብሎ ስለሰጋ፤ ከወዲሁ በህዝቡ ስነ ልቦና ላይ ተጽእኖ በማድረግ፣ ድሮም ያልነበረ ውክልና በመቀነስ እና በጀት በመቁረጥ የሚያዳክም መስሎት ነው። ሰሞኑን የእኩልነት ጥያቄ ያነሱ በነበሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ እና የነሱን ፈለግ ይከተላሉ ተብለው በተጠረጠሩ የአማራ ብሔር አባላት ላይ እየተፈጸመ ያለው እስራት፣ ድብደባና ግፍም የዚሁ ዘመቻ አካል ነው። አንድ ወያኔ ያልገባው ነገር ቢኖር ግን፣ በዘረኛ አገዛዙ የተንገፈገፈው የአማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ነው። በወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ላይ የተነሳው ተቃውሞ የህዝብ ቁጥር በማሳነስ፣ በጀት በመቁረጥ እና ስራው ዝም ብሎ ለወያኔ እጅ ማውጣት በሆነው ፓርላማ ተብዬ የመቀመጫ ድርሻን በመቀነስ የሚቆም አይደለም።" ብለዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org